# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
# የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ

## የግል የጽዳት ድርጅቶች የአሰራርና ድልድል መመሪያ ቁጥር 23/2013

## 1.መግቢያ

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግል የጽዳት ድርጅቶች የአሰራርና ድልድል መመሪያ**

በከተማችን አዲስ አበባ የሚመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ ሰብስቦ ለማጓጓዝ በመንግስት አቅም ብቻ ሊሰራ የማይችል በመሆኑ መንግስት የግል ባለሀብቱ በዘርፉ እንዲሰማራ በፈጠረው ምቹ ሁኔታ መሰረት በርካታ የግል የጽዳት ድርጅቶች በህጋዊ መንገድ ተመዝግበው ደረቅ ቆሻሻን ከተለያዩ ተቋማት በመሰብሰብ የማጓጓዝ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛል፡፡

ነገር ግን እነዚህ የግል የጽዳት ድርጅቶች ለማስተዳደር የሚያስችል የአሰራር መመሪያ የሌለ በመሆኑ ለተለያዩ ቅሬታዎች መነሻ እየሆነ ይገኛል፡፡ በተለይ በአሁኑ ሰዓት ከጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ጋር ውል ተፈራርመው ደረቅ ቆሻሻን ሰብስበው የሚያጓጉዙ የግል የጽዳት ድርጅቶች በከተማው ውስጥ የሚገኙትን አብዛኛውን ተቋማት ተከፋፍለው የያዙ በመሆናቸው አዲስ በዘርፉ ለሚሰማሩ የግል የጽዳት ድርጅቶች የፍትሀዊነት ጥያቄ እያስነሳ ይገኛል፡፡ ስለዚህ ይህንን ችግር በዘላቂነት በመፍታት በዘርፉ ግልጽና ፍትሀዊ ተጠቃሚነት ለመፍጠር ያስችል ዘንድ የግል የጽዳት ድርጅቶች ሊመሩበት የሚችል የአሰራር መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሻሻለ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፶/፪ሺ፲ አንቀጽ ፴፫ መመሪያ የማውጣት ሥልጣን በተመለከተ ለኤጀንሲው በከተማው ካቢኔ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን የግል የጽዳት ድርጅቶች የአሰራርና የድልድል መመሪያን አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

- ይህ መመሪያ **"በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግል የጽዳት ድርጅቶች የአሰራርና ድልድል መመሪያ ቁጥር ፳፫/፪ሺ፲፫** " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ዓላማ

- የግል የጽዳት ድርጅቶች ድልድልና አሰራርን ዘመናዊ፣ ግልጽና ፍትሀዊ በማድረግ አሰራሩን በማዘመን ከተማዋን ጽዱ ማድረግ ነው፡፡

### ፫. የቃላት ትርጓሜ

የቃላት አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጣቸው በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡

፪. **"ኤጀንሲ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፡፡

፫. **"ደረቅ ቆሻሻ"** ማለት ከንግድ፣ ከኢንዱስትሪ፣ ከተለያዩ ተቋማት፣ ከጋራዥ፣ ከግብርና፣ በእንስሳት የሚፈጠር ጥቅም የማይሰጥ ወይም የማይፈለግ ተብሎ የሚጣል ጠጣርና ከፊል ጠጣር የሆነ ቁስ ነው፡፡

፬. **"መሰብሰብና ማጓጓዝ"** ማለት ከመኖሪያ ቤት ውጭ ደረቅ ቆሻሻን ከተቋማት (ከሆቴል፣ ከንግድ ማዕከላት፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ወዘተ) ሰብስቦ ወደ ማቃጠያ ማዕከል፣ ወይም መልሶ መጠቀምና ኡደት ማዕከላት ወይም ማስወገጃ ቦታ በራስ ተሽከርካሪ ማጓጓዝ ነው፡፡

፭. **"የግል የጽዳት ድርጅት"** ማለት ደረቅ ቆሻሻን በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ የተለያዩ ተቋማት የመሰበሰብና የማጓጓዝ አገልግሎት የሚሰጡ በግል፣ በማህበር፣ በሽርክና፣ በዩኒዬን፣ ወዘተ የተደራጀ ድርጅት ነው፡፡

፤. "**ተሽከርካሪ**" ማለት ደረቅ ቆሻሻን ወደ ማስወገጃ ቦታ ወይም ማቃጠያ ማዕከል የሚጓጓዝበት የግል የጽዳት ድርጅት ኮምፓክተር ተሽከርካሪ ነው፡፡

፰. "**የስራ ፈቃድ**" ማለት የደረቅ ቆሻሻ አስተዳዳር ኤጀንሲ ለግል የጽዳት ድርጅቱ የሚሰጠው በከተማው ውስጥ ደረቅ ቆሻሻ የመሰብሰብና የማጓጓዝ የኮንትራት ስራ ውል ስምምነት ነው፡፡

፱. "**ተቋም**" ማለት በከተማችን ውስጥ ከመኖሪያ ቤት ውጭ የሆኑ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የንግድ ማዕከላት፣ ሆቴሎች፣ ሆስፒታሎች፣ ትናንሽ የንግድ ቤቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የመንግስት መስሪያቤቶች፣ ወዘተ ያጠቃልላል፡፡

## ፬. መመሪያውን ማውጣት ያስፈለገበት ምክንያት፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ተቋማት ደረቅ ቆሻሻን ለመሰብሰብና ለማጓጓዝ የተሰማሩ የግል የጽዳት ድርጅቶች የሚመሩበት ምንም ዓይነት የአሰራር መመሪያ የሌለ በመሆኑ ነባሮችንም ይሁን አዲስ ወደ ዘርፉ የሚገቡ የግል የጽዳት ድርጅቶችን ለማስተዳደር አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡

በሌላ በኩል እስከ አሁን የሚደረገው የግል የጽዳት ድርጅት ድልድል የፋይናንስ ስርዓት የተከተለ አለመሆኑና በውድድር የኮንትራት ስራው የማይሰጥ በመሆኑ ተጠያቂነት የሚያስከትል የአገልግሎት አሰጣጥ መሆኑ፡፡ በተጨማሪም ነባሮቹ የግል የጽዳት ድርጅቶች አብዛኛውን የስራ ቦታን ቀድመው የያዙት ሲሆን አዲስ በዘርፉ ደረቅ ቆሻሻ ለመሰብሰብና ለማጓጓዝ ለሚሰማሩ የግል የጽዳት ድርጅቶች ግልጽና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ለማስተናገድ አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡

ስለዚህ ይህ መመሪያ ግልጽና ፍትሀዊ የግል የጽዳት ድርጅቶች ድልድል ለማድረግና በተጨማሪም አዲስ በዘርፉ የሚገቡ የግል የጽዳት ድርጅቶች ያለምንም ችግር በመመሪያው መሰረት እንዲስተናገዱ ትልቅ አስተዋጾ ያበረክታል፡፡

## ፭. የመመሪያው ወሰን

- የዚህ መመሪያ ወሰን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በሚሰሩ በሁሉም የግል የጽዳት ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ፪. ደረቅ ቆሻሻን በኮንትራት ስራ ለመሰብሰብና ለማጓጓዝ የመመዝገቢያ መስፈርት

፩. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት ደረቅ ቆሻሻ ለመሰብሰብና ለማጓጓዝ የኮንትራት ስራ ላይ ለመወዳደር የሚከተሉትን መስፈርቶችን ማሟላት ይገባል፡፡

1.1 ከዚህ በፊት ከኤጀንሲው ጋር ውል ገብቶ ደረቅ ቆሻሻን ከተቋማት ሲሰበስብና ሲያጓጉዝ የቆየ የግል የጽዳት ድርጅት ከሆነ ከክፍለ ከተማ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት መልካም ስራ ለመስራቱ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ፡፡

1.2 ከዚህ በፊት ከኤጀንሲው ጋር ውል ገብቶ ደረቅ ቆሻሻን ከተቋማት ሲሰበስብና ሲያጓጉዝ የቆየ የግል የጽዳት ድርጅት ከሆነ ከማስወገጃ ቦታ፣ ከደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያና መልሶ መጠቀም ማዕከላት በአሰራር ላይ ችግር የሌለበት ወደ ማስወገጃ ቦታ እንዳይገቡ የተከለከሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን የማያስገባ ለመሆኑ የድጋፍ ደብዳቤ ያለው

1.3 በዘርፉ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያለው

1.4 በድርጅቱ ወይም በድርጅቱ ባለቤት ስም የተመዘገበ የስሪት ዘመኑ 20 ዓመት ያልበለጠው ቢያንስ ሁለት ኮምፓክተር ተሽከርካሪ ሊብሬ ያለው፡፡ ነገር ግን አንድ ተሽከርካሪ ብቻ ያለው ድርጅት ከሆነ ከሌላ አንድ ተሽከርካሪ ካለው ድርጅት ጋር በመሆን በራሳቸው ፍላጎት ተዋህደው በጋራ ተቀናጅተው ለመስራት የውል ስምምነት ይዘው መቅረብ ይገባቸዋል፡፡ ነገር ግን የኤጀንሲው የኮንትራት ውሉ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የተዋሃዱ ድርጅቶች በጋራ የመስራት ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

1.5 በድርጅቱ ወይም በግለሰቡ የተመዘገቡት ተሽከርካሪዎች ቀለማቸው ሰማያዊ እና ጂፒኤስ (GPS) የተገጠመላቸው ሆኖ ጂፒኤሱ አገልግሎት የሚሰጥ ለመሆኑ በኤጀንሲው ባለሙያዎች የተረጋገጠበት ማስረጃ ማቅረብ፡፡

1.6 በድርጅቱ የሚሰሩ የሰው ኃይል ብዛት ዝርዝር መረጃ

1.7 ድርጅቱ የሚገኝበት ቋሚ ቢሮ አድራሻ (ክፍለ ከተማው፣ ወረዳው፣ የቤት ቁጥሩ፣ ስልክ ቁጥር) እንዲሁም ቢሮው በኪራይ ከሆነ የኪራይ ውል ማስረጃ፡፡

1.8 ዓመታዊ የተሽከርካሪ ቴክኒካል ምርመራ ውጤትና የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ የተከፈለበት ሰነድ፡፡

1.9 ደረቅ ቆሻሻ የሚሰበስቡ ሰራተኞች፣ ሹፌርና ረዳት የቴታነስ ክትባትና የጤና ምርመራ ማስረጃ

1.10 ለምዝገባ ያመጣቸው ተሽከርካሪዎች ተበላሽተው ያልቆሙና ስራ መስራት የሚችሉ መሆናቸውን በኤጀንሲው ባለሙያዎች የተረጋገጠ ማስረጃ፡፡

፪. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት በዚህ አንቀጽ በቁጥር ፩ ከተዘረዘሩት ውስጥ ከ1.1 - 1.10 የተዘረዘሩትን ሙሉ በሙሉ ካላሟላ ድልድሉ ውስጥ አይገባም፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፪ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ አዲስ ገቢ ድርጅት ከሆነ ግን በቁጥር ፩ ከተዘረዘሩት ውስጥ ከ1.3 — 1.10 ያሉትን ማሟለት ይገባዋል፡፡

## ፯. የግል ጽዳት ድርጅት ደረቅ ቆሻሻ የመሰብሰብና የማጓጓዝ የኮንትራት ስራ ውድድር ምዝገባ

፩. ኤጀንሲው በየሁለት ዓመቱ ግልጽ የአገልግሎት ጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት የግል የጽዳት ድርጅቶች ደረቅ ቆሻሻን ከተቋማት በኮንትራት ስራ ለመሰብሰብና ለማጓጓዝ እንዲወዳደሩ ያደርጋል፡፡

፪. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት ደረቅ ቆሻሻን ከተቋማት በኮንትራት ለመሰብሰብና ለማጓጓዝ ሲወዳደር ኤጀንሲው በእጣ በሚመድበው በየትኛውም ወረዳና የስራ ቦታ የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

፫. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት በኮንትራት ስራው ሲወዳደር (ሲመዘገብ) በአንቀጽ ፮ ቁጥር ፩ በተዘረዘሩ መስፈርቶችን መሰረት ሁሉንም የተጠየቁ ሰነዶችን ጠርዞ ማህተም ባለው ሽኝ ደብዳቤና በእያንዳንዱ የሰነዱ ገጽ ጀርባ ላይ የድርጅቱን ማህተም በማሳረፍ በፖስታ በማሸግ ኤጀንሲው በሚያዘጋጀው የታሸገ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይገባዋል፡፡

፬. የግል የጽዳት ድርጅት የኮንትራት ስራ የምዝገባ ጊዜ በሁለት ዓመት አንዴ ሆኖ የምዝገባ ቀኑ ርዝመትም በማስታወቂያው በሚገለፀው የቀን መጠን ርዝመት የሚወሰን ይሆናል፡፡

፭. የማንኛውም አዲስ የግል የጽዳት ድርጅት ምዝገባ የሚከናዎነው በሁለት ዓመት አንዴ በግልጽ ማስታወቂያ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ምንም ዓይነት ምዝገባ በኤጀንሲው ማከናዎንና ድልድል መስጠት ክልክል ነው፡፡

፮. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፬ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ኤጀንሲው የግል የጽዳት ድርጅቶች እጥረት ካጋጠመው ወይንም በዲሲፕሊን ችግር ምክንያት የግል ጽዳት ድርጅቶችን ውል ካቋረጠና ውሉ የተቋረጠባቸው የግል ጽዳት ድርጅት ሲሰራበት የነበረው ቦታ ክፈተት ከፈጠረ በማናጅምንት አስፈቅዶ ግልጽ ማስታወቂ በማውጣት ሁለት ዓመት ሳይሞላው በማንኛውም ጊዜ አዲስ ድርጅት ምዝገባ አድርጎ በክፍት ቦታው ብቻ ድልድል ሊያደርግ ይችላል ወይንም ዝቅተኛ ተቋማት ባለበት ወረዳ የሚሰሩ የግል ጽዳት ድርጅቶችን አወዳድሮ ሊደለድል ይችላል፡፡

## ፯. በኤጀንሲው የውድድር ማስታወቂያ ከመውጣቱ በፊት የሚከናዎኑ ስራዎች

፩. የኤጀንሲው የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት በየሁለት ዓመቱ ድልድል ከመከናዎኑ ከ6 ወራት አስቀድሞ በ10 ሩም ክፍለ ከተማ የሚገኙ ተቋማትን መረጃ በየወረዳው ያደራጃል፡፡

፪. የተደራጀውን የተቋማት መረጃ መነሻ በማድረግ ተቋማት ሊያመነጩት በሚችል የቆሻሻ መጠን መነሻ በማድረግ በየወረዳቸው በሶስት ደረጃ እንዲከፈሉና እንዲደራጁ ይደረጋል፡፡ እነርሱም ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ ቆሻሻ ሊያመነጩ የሚችሉ በማለት ነው፡፡

፫. የቴክኒካልና ድልድል ኮሚቴው ወረዳዎች ባላቸው የተቋማት ብዛት በሶስት ደረጃ በመክፈል (ከፍተኛ ተቋማት ያላቸው፣ መካከለኛ ተቋማት ያላቸው፣ ዝቅተኛ ተቋማት ያለቸው) በማለት ወረዳዎችን ለእጣ ድልድል ዝግጁ ያደርጋል፡፡

፬. በየሁለት ዓመቱ የግል የጽዳት ድርጅት ድልድል ምዝገባ ከመከናዎኑ በፊት የኤጀንሲው የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት በስራ ላይ የሚገኙ ድርጅቶች አገልግሎት ለሚሰጡት ተቋም ምንያክል በጥራት አገልገሎት እየሰጡ እንደሆነ በጥናት መረጃውን በማደራጀት የምደባ መስፈርት እንዲሆን ይደረጋል፡፡

፭. በየሁለት ዓመቱ የግል የጽዳት ድርጅት ድልድል ምዝገባ ከመከናዎኑ በፊት የኤጀንሲው የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት በስራ ላይ

የሚገኙ ተሽከርካሪዎች በመመሪያው መስፈርት መሰረት ጂፒኤስ መገጠሙን፣ የተሽከርካሪው ቀለም፣ በተሽከርካሪው ላይ የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ሳጥን ከነሙሉ ግብዓቱ መኖሩን፣ ተሽከርካሪው ተበላሽቶ ያልቆመና በስራ ላይ ለመሆኑ በማረጋገጥ በደብዳቤ ለድርጅቱ ማሳወቅ ይጠበቅበታል፡፡

፫. የኤጀንሲው የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት በየሁለት ዓመቱ ለሚያደርገው ድልድል ምን ያክል ተሽከርካሪ እንደሚያስፈልገው የወረዳዎችን የተቋማት ብዛትና የቆሻሻ የማመንጨት አቅም ግምት በማስገባት የምዝገባ ማስታወቂያ ከመውጣቱ በፊት በማናጅምንት እንዲወሰን ያደርጋል፡፡

## ፱. የቴክኒካልና ድልድል ኮሚቴ አመራረጥ

፩. በኤጀንሲ የግል የጽዳት ድርጅቶች ለኮንትራት ስራ ለመወዳደር ያስገቡትን ሰነድ ቴክኒካል ምዘና እና ድልድል የሚያደርግ አንድ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡ ይህ ማለት የቴክኒካል ግምገማውንና ድልድሉን የሚያደርገው ይህ ኮሚቴ ብቻ ይሆናል ማለት ነው፡፡

፪. የድልድል ኮሚቴው የሚመረጠው በተቋሙ ስራ አስኪያጅና ምክትል ስራ አስኪያጅ ሆኖ በማናጅመንት እንዲጸድቅ መደረግ ይገባዋል፡፡

፫. የግል የጽዳት ድርጅት የቴክኒካል ምዘናና ድልድል ኮሚቴ አምስት አባላት አሉት፡፡ እነርሱም

| ተ.ቁ | የምደባ ኮሚቴ አባላት | ብዛት | በኮሚቴው ያለው ድርሻ |
|---|---|---|---|
| 1 | የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት | 1 | ሰብሳቢ |
| 2 | ን/ግ/ጠ/አገ/ ዳይሬክቶሬት | 1 | ፀሀፊ |
| 3 | የለውጥ ቡድን | 1 | አባል |
| 4 | ኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት | 1 | አባል |
| 5 | ላንድፊል ዳይሬክቶሬት | 1 | አባል |

## ፲. የቴክኒካል ምዘናና ድልድል ኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

፩. የማንኛውም የቴክኒካልና የድልድል ኮሚቴ አባል የስራ ዘመን ለአንድ ዙር ሆኖ ነገር ግን ማናጅምንቱ ካመነበትና ካጸደቀው እስከ ሶስት ዙር እንዲቀጥሉ ይደረጋል፡፡ ነገር ግን ከሶስት ዙር በላይ እንዲሰሩ አይገደዱም

፪. ማንኛውም የቴክኒካልና የምደባ ኮሚቴ አባል የተቋሙን ጥቅም አሳልፎ ሲሰጥ ከተገኘ፣ የኮሚቴውን ሚስጥር ካወጣ፣ ከመመሪያው ውጭ ሲሰራ ከተገኘ፣ የተቋሙ ስራ አስኪያጅ ችግሩን ለማናጅምንት አቅርቦ አባሉ ከኮሚቴነት እንዲነሳ ያደረጋል፡፡ በምትኩም ሌላ አባል በማናጅምንት እንዲፀድቅ ይደረጋል፡፡

፫. የቴክኒካል ምዘናና ምደባ ኮሚቴው ለውድድር የሚቀርቡ የግል ጽዳት ድርጅቶችን በዚህ መመሪያ በአንቀጽ ፺ ቁጥር ፩ በቀረበው መስፈርት መሰረት የቴክኒካል ምዘናውን ያከናውናል ውጤቱንም ለማናጅምንት አቅርቦ ያፀድቃል፡፡

፬. በቴክኒካል ምዘናው ያላላፉ ድርጅቶች ወይንም ድርጅቱ አልፎ ነገር ግን ድርጅቱ በርካታ ተሸከርካሪዎችን አቅርቦ ከመሀል በቴክኒካል ምዘናው ያላላፈ ተሽከርካሪ ካለ ውጤቱ በማናጅመንት እንዲፀድቅ በማድረግ ተሽከርካሪው ወይም ድርጅቱ ያልተመረጠበት ምክንያት ተጠቅሶ ውጤቱ ለተወዳደሩ ድርጅት እንዲያውቀው በደብዳቤ እንዲገለጽላቸው ያደርጋል፡፡

፭. የቴክኒካል ምዘናውን ያለፉ ድርጅቶች ተወዳዳሪዎችና ታዛቢዎች በተገኙበት በወረዳ ተከፋፍሎ በእጣ እንዲደለደሉ ያደረጋል፡፡

፮. የቴክኒካል ኮሚቴው የድልድል ውጤቱን በቃለ ጉባኤ አደራጅቶ ለተቋሙ የበላይ ኃላፊ እንዲያፀድቀው ያደርጋል፡፡ የድልድሉ ውጤት በተቋሙ የበላይ ኃላፊ ከፀደቀ በኋላ በማስታወቂያ መለጠፊያ ላይ እንዲለጠፍ ያደርጋል፡፡

## ፲፩. የግል የጽዳት ድርጅት የኮንትራት ስራ የእጣ ድልደል አወጣጥ

፩. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅቶች እጣ ድልድል ውስጥ የሚገባው ቴክኒካል ምዘናውን ሙሉ በሙሉ ካለፈ ብቻ ነው፡፡

፪. የማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት የእጣ ድልድል የሚከናዎነው የግል የጽዳት ድርጅቱ በሚያስገባው የተሽከርካሪ ታርጋ ነው፡፡ ይህም ማለት አንድ የግል የጽዳት ድርጅት 10 ተሽከርካሪ ቢኖረውና አስሩም የቴክኒካል ምዘናውን ካለፉ ከሌሎች የግል ጽዳት ድርጅት ቴክኒካል ምዘናውን ካለፉ ተሽከርካሪዎች ኤጀንሲው በሚያስቀምጠው ደረጃ መሰረት በእጣ ለተሽከርካሪዎቹ ምደባ ይሰጣል፡፡ በዚህም አስሩም ተሽከርካሪዎች በአስሩም ክፍለ ከተማ በተለያዩ ወረዳዎች ሊመደቡ ይችላሉ ወይንም የተወሰኑ ተሽከርካሪዎች እጣ ሳይወጣላቸው ሊቀር ይችላል፡፡

፫. ለግል የጽዳት ድርጅቶች የእጣ ድልድል የሚከናዎነው በወረዳ ተከፋፍሎ ሲሆን ከፍተኛ ተቋማት ያለባቸው ወረዳዎች ካሉ ለሁለት ወይም ከሁለት በላይ በቀጠና ወይም በመንደር ተከፍለው ለእጣ እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡

፬. ቴክኒካል ምዘናውን አልፎ በእጣ ድልድል ተወዳድሮ ምደባ ያላገኘ ማንኛውንም የግል የጽዳት ድርጅትን ኤጀንሲው የመመደብ ግዴታ የለበትም፡፡ ይህ ማለት ኤጀንሲው እጣ ድለድል የሚሰጠው በሚያስፈልገው የተሸከርካሪ መጠን ብቻ ነው፡፡

፭. የተሸከርካሪዎች የእጣ አወጣጥ ድልድል ከዚህ በታች በቀረበው መሰረት ይሆናል፡፡

- የመጫን አቅሙ ከ45 ሜ.ኩብ በላይ የሆነ ተሸከርካሪ ከፍተኛ ተቋማት ብዛት በሚገኝበት ወረዳ በእጣ እንዲወዳደር ይደረጋል፡፡
- የመጫን አቅማቸው ከ26 — 45 ሜትር ኩብ የሆነ ተሸከርካሪ መካከለኛ የተቋማት ብዛት በሚገኙበት ወረዳ በእጣ እንዲወዳደር ይደረጋል፡፡
- የመጫን አቅማቸው 8 — 25 ሜትር ኩብ የሆነ ተሸከርካሪ ዝቅተኛ የተቋማት ብዛት ባለበት ወረዳ ላይ ለእጣ እንዲወዳደር ይደረጋል፡፡

፮. ኤጀንሲው መዝግቦ ባቀረበው የተቋማት ዝርዝር መሰረት ሁሉም ወረዳዎች ባላቸው የተቋማት ብዛት በተለይ ከፍተኛ ቆሻሻ ያመነጫሉ በሚባሉ ተቋማት ብዛት መሰረት በማድረግ ወረዳዎች በሶስት ደረጃ እንዲከፈሉ ይደረጋል፡፡ እነሱም ዝቅተኛ ተቋም ብዛት ያለው ወረዳ፤ መካከለኛ ተቋም ብዛት ያለው ወረዳና ከፍተኛ ተቋም ብዛት ያለው ወረዳ ናቸው፡፡

፯. በዚህ አንቀጽ ቀጥር ፫ በተገለፀው መሰረት የኤጀንሲው የቴክኒካልና ድልድል ኮሚቴ በሚወስነው መጠን መሰረት እስከ ስንት ተቋማት ያላቸው ወረዳዎች ከፍተኛ፤ መካከለኛና ዝቅተኛ ይባሉ የሚለውን ይወስናል፡፡

## ፲፪. የስራ ውል መዋዋል

፩. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት የእጣ ድልድል ምደባ ካገኘ በኋላ ከኤጀንሲው ጋር ህጋዊ የስራ ውል መፈራረም ግዴታ አለበት፡፡

፪. ኤጀንሲው የእጣ ድልድል ካደረገ በኋላ የማንኛውንም የግል ጽዳት ድርጅት የቦታ ድልድል ለውጥ ማድረግ አይችልም፡፡ ነገር ግን ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት ከኤጀንሲው ጋር ውል ከመዋዋላቸው በፊት በግላቸው የምደባ ቦታ መቀያየር ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ለመቀያየራቸው የሁለቱም ድርጅቶች ማህተም ያለው እና ሁለቱም ፈልገው መቀያየራቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ለኤጀንሲው ማስገባት ይጠበቅባቸዋል፡፡

፫. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት በዕጣ በተደለደለበት ወረዳ ለመስራት ከኤጀንሲው ጋር ውል ከገባ በኋላ ምንም አይነት የቦታ ቅያሬ ማድረግ አይችልም፡፡

፬. የግል የጽዳት ድርጅት ደረቅ ቆሻሻ ከሚሰበስብበት ተቋም ጋር ኤጀንሲው በሚያዘጋጀው የውል ፎርም/ማኑፌስቶ/ አራት ኮፒ በመፈራረም ለደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ፣ ለክፍለ ከተማ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት፣ ቆሻሻ ለሚያነሳለት ተቋምና ቀሪውን ለእራሱ የማስቀመጥ ግዴታ አለበት፡፡

፭. የግል የጽዳት ድርጅቶች ከተቋማት ጋር የሚዋዋሉበትን የውል ሰነድ ኤጀንሲው ለሁሉም ወጥ በሆነ መልኩ እዲዘጋጅ ያደርጋል፡፡

፮. በአዲስ ድልድል ምክንያት በተቋማት የቆሻሻ መነሳት ችግር እንዳያጋጥም ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅቶች አዲስ በተመደቡበት ተቋም ሂዶ ውል ተዋውሎ ስራ አስከሚጀምር ድረስ አዲሱ ድልድል በደብዳቤ ከተሰጠው ቀን ጀምሮ ለአንድ ወር የዝግጅት ጊዜ ይሆናል፡፡

፯. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፮ በተገለፀው መሰረት ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት በአንድ ወር የዝግጅት ጊዜ ደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብ ያለበት ቀድሞ በተመደበበትና ሲሰራ በነበረው ተቋም ውስጥ ሆኖ ነገር ግን ጎን ለጎን አዲስ በተመደበበት ተቋም በመሄድ ውል መግባትና ራሱን ማስተዋወቅ ይገባል፡፡ ነገር ግን የድልድል ደብዳቤ ከተሰጠው ከአንድ ወር በኋላ ከዚህ በፊት ሲሰራበት የነበረውን ተቋም አዲስ ለተመደበው የግል ጽዳት ድርጅት አስረክቦ አዲስ በተደለደለበት ተቋም ብቻ አገልግሎት መስጠት ይገባዋል፡፡

## ፲፫. የስራ ውል ፈቃድ እድሳት

፩. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት የስራ ውል ፈቃድ በኤጀንሲው በየዓመቱ የማሳደስ ግዴታ አለበት፡፡

፪. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት የስራ ውል ፈቃድ እድሳት ከሀምሌ 1-30 ማከናዎን አለበት፡፡ ይህም ማለት የሀምሌ ወር ክፍያ ከመከናዎኑ በፊት ሁለቱም ተዋዋዬች ውላቸውን ማደስና መፈራረም ይገባል፡፡

፫. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት የስራ ውል ፈቃዱ ከኤጀንሲው ጋር ለማደስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት ይገባዋል፡፡

- ከክፍለ ከተማ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት በስራው እንዲቀጥል የድጋፍ ደብዳቤ
- ከማስወገጃ ቦታ፤ ከመልሶ መጠቀም ማዕከላት ወይም ከደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ ማዕከል በአሰራር ላይ ችግር የሌለበት ለመሆኑ ኤጀንሲው በሚያዘጋጀው ቼክ ሊስት መሰረት የድጋፍ ደብዳቤ
- የታደሰ የንግድ ፈቃድ
- ዓመታዊ የተሽከርካሪ ቴክኒካል ምርመራ ውጤት
- የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ
- ደረቅ ቆሻሻ የሚሰበስቡ ሰራተኞች የጤና ምርመራ ውጤት
- የታደሰ የቤት ኪራይ ውል ወይም ቢሮው የሚገኝበት ካርታ
- በተሽከርካሪው ውስጥ የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ሳጥን ከነሙሉ ግብዓቱ
- ጂፒኤስ የተገጠመለት ተሽከርካሪ ስራ ላይ መሆኑና ጂፒኤሱ ስራ ላይ መሆኑ

፬. የግል የጽዳት ድርጅት የስራ ውል ፈቃድ በኤጀንሲው በየዓመቱ ካልታደሰ የስራ ውል ፈቃዱ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይሰረዛል፡፡

## ፲፬. የግል የጽዳት ድርጅት የአገልግሎት ክፍያ ስርዓት

፩. የግል የጽዳት ድርጅት ደረቅ ቆሻሻ ሰብስቦ ላጓጓዘበት የክፍያ ተመን የከተማው አስተዳደር በሚወስነው ቁርጥ ዋጋ መሰረት በሜትር ኩብ ወይም በኪሎ ግራም ተሰልቶ ይሆናል፡፡

፪. የግል የጽዳት ድርጅት ሰብስቦ ላጓጓዘት የደረቅ ቆሻሻ ክፍያ በወሩ መጨረሻ የክፍለ ከተማው ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት ያረጋገጠበት ሰነድ፤ ከማስወገጃ ቦታ የቀረበ መረጃና የተቋማት መረጃ ተመሳክሮ ይከፈላል፡፡

፫. ለግል የጽዳት ድርጅቶች ሰብስበው ለሚያጓጉዙበት ክፍያ ተመን ዋጋ በጥናት የተመሰረተና ከወቅቱ ሁኔታ ጋር ያገናዘበ የዋጋ ተመን የከተማው አስተዳደር ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡

፬. ማንኛው የግል የጽዳት ድርጅት የማስወገጃ አገልግሎት ክፍያ ኤጀንሲው በሚያወጣው ታሪፍ መሰረት የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

፭. በከተማው በሚገኑ በሁሉም ተቋማት በግል ጽዳት ድርጅቶች ለሚሰበሰብና ለሚጓጓዝ የደረቅ ቆሻሻ የክፍያ መጠኑ ተመሳሳይ ነው፡፡

፮. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት ውል ተዋውሎ ስራ ከጀመረ በኋላ የክፍያ ማሻሻያ መጠየቅ አይችልም፡፡ ነገር ግን የውል እድሳት ከመፈራረሙ በፊት ክፍያው እንዲሻሻልለት በመጠየቅ ተዋውሎ ስራ መጀመር ይገባዋል፡፡

## ፲፭. የግል ጽዳት ድርጅት ደረቅ ቆሻሻ መሰብሰቢያና ማጓጓዣተሽከርካሪ ሁኔታ

፩. በከተማችን ደረቅ ቆሻሻ የሚሰበስቡ የግል የጽዳት ድርጅቶች ተሽከርካሪ ጂፒኤስ የተገጠመለት ኮምፓክተር ብቻ መሆን ይገባዋል፡፡ ነገር ግን ተቋማት ከሚያመነጩት ደረቅ ቆሻሻ ባህሪ ተነስቶ ኤጀንሲው በልዩ ሁኔታ የገንዳ ተሽከርካሪ ለተወሰኑ ተቋማት ብቻ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፪. ደረቅ ቆሻሻ የሚሰበስብ የግል የጽዳት ድርጅት ተሽከርካሪ ቀለም ሰማያዊ ሊሆን ይገባል፡፡

፫. የግል የጽዳት ድርጅት ተሽከርካሪ ላይ የድርጅቱ ስም በሁለቱም ጎን የተጻፈበት ሊሆን ይገባዋል፡፡

፬. የግል የጽዳት ድርጅት በስራ ላይ የሚሰማራ ተሽከርካሪ የስሪት ዘመኑ ከ20 ዓመት ያልበለጠው መሆን ይገባዋል፡፡

፫. ደረቅ ቆሻሻን በኮንትራት ለመሰብሰብና ለማጓጓዝ የሚመዘገብ የግል ጽዳት ድርጅት ቢያንስ ሁለት ኮምፓክተር ተሽከርካሪ በድርጅቱ ስም ወይም በድርጅቱ ባለቤት ስም ሊኖረው ይገባል፡፡ ነገር ግን አንድ ተሽከርካሪ ብቻ ያለው ድርጅት ከሆነ ከሌላ አንድ ተሽከርካሪ ካለው ድርጅት ጋር በመሆን በራሳቸው ፍላጎት ተዋህደው በጋራ ተቀናጅተው ለመስራት የውል ስምምነት ይዘው መቅረብ ይገባቸዋል፡፡ ነገር ግን የኤጀንሲው የኮንትራት ውሉ አስከሚጠናቀቅ ድረስ የተዋሃዱ ድርጅቶች በጋራ የመስራት ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ቁጥር ፫ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ሁለት ኮምፓክተር ተሽከርካሪ ከሌለውና አንድ ብቻ ተሽከርካሪ ኖሯቸው በጋራ ለመስራት የተስማሙ ሁለት ድርጅቶች  ክፍያም ይሁን ከኤጀንሲው ጋር ውል ሲዋዋሉ ለየብቻቸው በየግል ተቋማቸው ሆኖ ክፍያም የሚከፈላቸው በየግል ተሽከርካሪያቸው በሰራው መጠን በግል ድርጅታቸው ስም ነው፡፡ ነገር ግን የእነዚህ ድርጅቶች የጋራ ስምምነት ውል ዋና አላማው የአንደኛው ተሽከርካሪ ቢበላሽ የሌላኛው ድርጅት ሸፍኖ እንዲሰራ ለማድረግ ነው፡፡

፭. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት ተሽከርካሪ ከመግዛቱ በፊት በቅድሚያ ኤጀንሲውን በደብዳቤ መጠየቅና ለመግዛት የድጋፍ ደብዳቤ ከኤጀንሲው ማግኘት አለበት፡፡ ነገር ግን ከኤጀንሲው እውቅና ውጪ በግላቸው ተሽከርካሪ ገዝተው ኤጀንሲው ወደ ስራ እንዲያስገባላቸው የሚጠይቁ የህብረት ሽርክና ማህበራትም ይሁን የግል ድርጅት ኤጀንሲው አያስተናግድም፡፡

፮. በስራ ላይ የሚገኝ ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት ስራ ከጀመረ በኋላ ከኤጀንሲው እውቅና ውጪ ተጨማሪ ተሽከርካሪ ገዝቶ ወደ ስራ ማስገባት ወይም እንዲገባለት መጠየቅ አይችልም፡፡

## ፲፬. የደህንነት መጠበቂያና ግብዓት ስለማሟላት

፩. ማንኛው የግል የጽዳት ድርጅት ደረቅ ቆሻሻን ሲሰበስብና ሲያጓጉዝ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳዳር ኤጀንሲ በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት ሁሉም ሰራተኞች የደህንንት መጠበቂያ ግብዓት፤ ቱታና ባጅ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡

፪. የማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት ሹፌር፣ ረዳት፣ ደረቅ ቆሻሻ የሚጭን ሰራተኛ በስራ ላይ በሚሆንበት ወቅት ውሃ ሰማያዊ ቀለም ያለው ቱታ፣ ቀይ አንጸባራቂ ጃኬት፣ ማስክ፣ ጓንትና ሴፍቲ ጫማና ባጅ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፫. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት ደረቅ ቆሻሻ የሚሰበስቡ ሰራተኞች ቱታ ሁሌም ንፁህ መሆን ይገባል፡፡

## ፲፮. የስራ አገልግሎትን ውል ስለመሰረዝ

፩. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት የአካባቢ ጥበቃ ህጎችን ከተላለፈ ወይም የደረቅ ቆሻሻ ህግ፣ ደንብ፣ ከተላለፈ የተሰጠው የስራ ውል ፈቃድ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይሰረዛል በህግም ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፪. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት በአቅም ማነስ፣ ስራው ባያዋጣው ወይም የሥራ ዘርፉን በመቀየር አስቦ በግሉ ሥራውን ለማቋረጥ ሲወስን ከሁለት ወር በፊት ለውል ሰጪው በጽሁፍ ማመልከቻውን በማቅረብ ውሉ እንዲቋረጥ ይደረጋል፡፡

፫. በማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት  ላይ የክፍለ ከተማው ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት በጽሁፍ ሁለቴ ቅሬታ ካቀረበበት፣ አገልግሎት በሚሰጣቸው በተለያዩ ደንበኞች ሁለቴ ቅሬታ ከቀረበበትና በማስወገጃ ቦታ ተደጋጋሚ ሁለቴ ቅሬታ ከቀረበበትና በኤጀንሲው ከተረጋገጠ፣ የስራ ውል ፈቃድ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ይቋረጣል፡፡

፬. ከተመደበበት ወረዳና ክፍለ ከተማ ውጭ ደረቅ ቆሻሻ ሲሰበስብና ሲያጓጉዝ ከተገኘ እንዲሁም ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወሰን ውጪ ደረቅ ቆሻሻ ሲያስገባ ከተገኘ ወይም ከሌሎች ጋር ተመሳጥሮ እንዲገባ ያደረገ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ውሉ ተቋርጦ በህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፭. ማንኛውም የግል ጽዳት ድርጅቶች ኤጀንሲው ከሚከፍላቸው ክፍያ ውጪ ከተቋማት ጋር ተደራድሮ ተጨማሪ ክፍያ ሲያስከፍል ከተገኘ እንዲሁም በአድማ በመሳተፍ አገልግሎት መስጠት ካቆመ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ውሉ ተቋርጦ በህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፮. ማንኛውም የግል ጽዳት ድርጅት የደረቅ ቆሻሻ ማጓጓዣ ኮምፓክተር ተሽከርካሪው የማመቅ ሲስተም/ ሀይድሮሊክ ሲስተም/ በትክክል መስራቱን አረጋግጦ ወደ ስራ

ማሰማራት አለበት፡፡ ነገር ግን ሲስተሙን አበላሽቶ ሲሰራ ከተገኘ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ውሉ ተቋርጦ በህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሶስት

# የተለያዩ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

## ፲፰. የኤጀንሲው ተግባርና ኃላፊነት

አግባብ ባላቸው ህጎች ለኤጀንሲው የተሰጡት ስልጣንና ኃላፊነት እንደተጠበቁ ሆኖ የግል የጽዳት ድርጅቶች የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና ማጓጓዝን በሚመለከት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባር ኃላፊነት አሉት፡፡

፩. የግል የጽዳት ድርጅቶች የሚሰሩበት የአሰራር ስታንዳርድ ያዘጋጃል፡፡

፪. በከተማው በግል ጽዳት ድርጅቶች አገልግሎት የሚያገኙና ማግኘት የሚገባቸውን ድርጅቶችን መረጃ ያደራጃል፡ ለእጣ ድልድል እንዲመች አድርጎ በየወረዳው ከፋፍሎ ያዘጋጃል፡፡

፫. ለግል የጽዳት ድርጅቶች በመመሪያው መሰረት ድልድል ይሰጣል፡ የስራ ውል ስምምነት ይፈራረማል፡፡ በውሉና በመመሪያው መሰረት የማይሰሩትን በማስረጃ ሲረጋገጥ የውል ፈቃዳቸውን ያለቅድመ ሁኔት ይሰርዛል፡፡

፬. የግል የጽዳት ድርጅት ክፍያን ከድርጅቱ የሚመጣ ሰነድን፤ ከማስወገጃ ቦታ የቀረበ ሰነድንና ከክፍለ ከተማ የቀረበ ማስረጃን አጣርቶ ክፍያ ይፈጽማል፡፡

፭. የግል የጽዳት ድርጅቶችን የስራ አፈጻጸም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ይገመግማል፤ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡

፯. የኮንትራት ውል በማዘጋጀት ወደ ጽዳት ስራ ሊገቡ የሚችሉ የግል የጽዳት ድርጅቶችን ውል ይፈራረማል፡ ስራው በውሉ መሰረት መሰራቱን ይከታተላል ይቆጣጠራል፡፡

፰. በዘርፉ ለተሰማሩ የግል የጽዳት ድርጅቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ይሰጣል፡፡

## ፲፱. የክፍለ ከተማ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት ተግባራና ኃላፊነት

፩. በክፍለ ከተማው ውስጥ የሚገኙትን በግል የጽዳት ድርጅቶች አገልግሎት ፈላጊ ተቋማት፣ ድርጅቶች፣ ሆቴሎች ወዘተ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ በክፍለ ከተማው ውስጥ በሚገኙ ወረዳዎች በተመደበ የግል ጽዳት ድርጅት እንዲነሳ ያደርጋል፡፡

፪. በክፍለ ከተማው ተመድበው ለሚሰሩ የግል የጽዳት ድርጅቶች ለሚሰጡት አገልግሎት በስታንዳርዱ መሰረት እየተሰራ ለመሆኑ ተከታታይነት ያለው ድጋፍ፣ ክትትል፣ ቁጥጥር ያደርጋል፡፡ የአፈጻጻማቸውን ሪፖርት አጠናክሮ ለኤጀንሲ ይልካል፡፡

፫. በክፍለ ከተማው የሚሰሩ የግል የጽዳት ድርጅቶች የሚፈጠር ችግርን፣ የተቋማት መቀማማትን ወዘተ ይፈታል፡፡

፬. ከተገልጋዩ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ለይቶ ወቅታዊ ምላሽ ይሰጣል፡፡ በክፍለ ከተማው ከሚገኙ ከግል የጽዳት ድርጅቶች ጋር በቋሚነት ስራዎችን ይገመግማል አስፈላጊውን ማስተካከያም በመሪያው መሰረት ያደርጋል፡፡

፭. በየወሩ የግል የጽዳት ድርጅቱ በተመደበበት ተቋም ለማገልገሉ አረጋግጦ የክፍያ ሰነዱ ተገቢ መሆኑን ለኤጀንሲው በሸኝ ደብዳቤ ይልካል፡፡

## ፳. የወረዳ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

፩. በወረዳው በግል የጽዳት ድርጅት አገልግሎት ፈላጊ ተቋማት፣ ድርጅቶች፣ ሆቴሎች ወዘተ መረጃዎችን ያሰባስባል፣ ያደራጃል፣ በግል ጽዳት ድርጅት እንዲነሳ ያደርጋል፡፡

፪. የግል የጽዳት ድርጅቶች በስታንዳርዱ መሰረት ለተመደቡበት ተቋም አገልግሎት መስጠታቸውን ይከታተላል፣ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ የአፈጻጻማቸውን ሪፖርት አጠናክሮ ለክፍለ ከተማው በየወሩ ይልካል፡፡

፫. በወረዳው የሚገኙ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ከመኖሪያ ቤት ውጭ (ከተለያዩ ተቋማት፤ የንግድ ድርጅቶች) ደረቅ ቆሻሻ እንዳያነሱ ግንዛቤ ይፈጥራል፤ ይከታተላል፤ ቆጣጠራል፤ አስፈላጊውን ማስተካከያ ይወስዳል፡፤

## ፳፩. የግል የጽዳት ድርጅት ተግባርና ግዴታ

፩. ማንኛውም የግል ጽዳት ድርጅት ወደ ማስወገጃ ቦታ፤ ማቃጠያ ማዕከላት ወይም ለመልሶ መጠቀምና ኡደት ማዕከላት የሚጓጓዙ ደረቅ ቆሻሻዎች ኤጀንሲ ባወጣው ደንብ፤ መመሪያ፤ ስታንዳርድና ማኑዋል መሰረት ማከናዎን ይገባዋል፡፡

፪. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት በየዓመቱ ከኤጀንሲው ጋር በዚህ መመሪያው መሰረት የስራ ውሉን ማደስና የመፈራረም ግዴታ አለበት፡፡

፫. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት ደረቅ ቆሻሻ ከሚያነሳለት ድርጅት ጋር ውል በመፈራረም ቆሻሻውን የሚያነሳበትን ቋሚ ፕሮግራም የማሳወቅና በፕሮግራሙ መሰረት የማንሳት ግዴታ አለበት፡፡

፬. የግል የጽዳት ድርጅቶች ከተቋማት ውጭ የቤት ለቤት ደረቅ ቆሻሻ የማሰባሰብና የማጓጓዝ ስራ ላይ መሳተፍ አይችሉም፡፡

፭. የግል ጽዳት ድርጅቶች የተረከቡትን ቆሻሻ የአካባቢና የጤና ችግር መንስኤ እንዳይሆን ተገቢውን ጥንቃቄ በመውሰድ የህብረተሰቡን ጤና እና የአካባቢ ደህንነት መጠበቅ አለባቸው፡፡

፮. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት ደረቅ ቆሻሻን ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወሰን ውጭ ሰብስቦ ወደ ከተማው ማስወገጃ ቦታ፤ የቆሻሻ ማቃጠያ ወይም የኮምፖስት ማዕከላት ማስገባት የተከለከለ ነው፡፡

፯. የግል የጽዳት ድርጅት ከኤጀንሲው ጋር የተዋዋለውን ውል ለማቋረጥ ሲፈልግ ከማቋረጡ በፊት አንድ ወር ሲቀረው ለውል ሰጪው በጽሁፍ ማሳወቅ ይገባዋል፡፡

፰. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅቶች በውሉ ተመላክቶ በተሰጠው የስራ ቦታ ብቻ አገልግሎቱን የመስጠት ግደታ አለበት፡፡

፱. የግል የጽዳት ድርጅቶች ያልተለየ ደረቅ ቆሻሻ ወደ ማስወገጃ ቦታ ይዘው መሄድ ስለማይችሉ አገልግሎት ለሚሰጧቸውን ተቋማት ቆሻሻን ከምንጩ እንዲቀንሱና በዓይነት የመለየት ስራ እንዲያከናውኑ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፲፩. የግል የጽዳት ድርጅቶች የመኪና መበላሸት ቢገጥመው በአፋጣኝ ሌላ መኪና በመመደብ አገልግሎቱ እንዳይቋረጥ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፲፪. የግል ጽዳት ድርጅቶች ኤጀንሲው ከሚከፍላቸው ክፍያ ውጪ ከተቋማት ጋር ተደራድሮ ምንም አይነት ተጨማሪ ክፍያ ማስከፈል የተከለከለ ነው፡፡

፲፫. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት ደረቅ ቆሻሻ የሚሰበስብበት ተቋም 5 ሜትር የዞን ጽዳት እንዲያፀዳ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፲፬. የግል የጽዳት ድርጅት አደገኛ ደረቅ ቆሻሻውን ከአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ፈቃድ ሳይኖረው ማጓጓዝም ይሁን መሰብሰብ አይችልም፡፡

፲፭. የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ ካስቀመጠው የማስወገጃ፣ የማቃጠያ ወይም የኮምፖስት ማዕከል ውጭ ከተቋማት የተሰበሰበን ደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ የተከለከለ ነው፡፡

፲፮. በማስወገጃ ቦታ፣ በማቃጠያ ወይም በኮምፖስት ማዕከላት የሚተገበሩ አሰራሮችንና ስታንዳርዶችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

፲፯. ማንኛውም የግል የጽዳት ድርጅት በወሩ ያጓጓዘውን ቆሻሻ መጠንና ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት የዋለ የቆሻሻ መጠንና ብር በየወሩ ለኤጀንሲውና ቆሻሻ ለሚሰበስብበት ክፍለ ከተማ ሪፖርት የማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

፲፯. ማንኛውም የግል ጽዳት ድርጅት የደረቅ ቆሻሻ ማጓጓዣ ኮምፓክተር ተሽርካሪው የማመቅ ሲስተም/ ሀይድሮሊክ ሲስተም/ በትክክል መስራቱን አረጋግጦ ወደ ስራ ማሰማራት አለበት፡፡

፲፰. ማንኛውም የግል ጽዳት ድርጅት የደረቅ ቆሻሻ ማጓጓዣ ኮምፓክተር ተሽርካሪው ንጽህና ቢያንስ በሳምንት አንድ ቀን መታጠብ አለበት፡፡

፲፱. ማንኛውም የግል ጽዳት ድርጅት አገልግሎት በሚሰጠው ተቋም የተለየውንና ለመልሶ መጠቀም የሚውለውን ደረቅ ቆሻሻ በማንሳት ለሚረከብ አካል መስጠት ወይም እራሱም መጠቀም አለበት፡፡

፳. የሰራተኞችን የደህንነት መጠበቂያ ግብዓት በስታንዳርዱ መሰረት ማሟላትና ንጽህናው እንዲጠበቅ በማድረግ የመስራት ግዴታ አለበት፡፡

## ፳፪. ቆሻሻ የሚያመነጭ ተቋም ተግባር

፩. ማንኛውም ተቋም ያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ በዓይነት በመለየት፣ ከምንጩ የመቀነስና ውል ገብቶ ቆሻሻ ለሚያነሳለት የግል የጽዳት ድርጅት የማስረከብ ግዴታ አለበት፡፡

፪. ማንኛውም ተቋም ያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ አካባቢን ሳይበክል ኤጀንሲው በሚያወጣው የማጠራቀሚያ ስታንዳርድ መሰረት የማጠራቀም ግዴታ አለበት፡፡

፫. ማንኛውም ተቋም ለግል የጽዳት ድርጅቶች ተጨማሪ ወይም በድርድር የሚከፍለው ምንም ዓይነት ክፍያ የለም፡፡

፬. ማንኛውም ተቋም ቆሻሻ ከሚሰበስብለት የግል የጽዳት ድርጅት ጋር ውል ተፈራርሞ ቆሻሻው እንዲነሳለት የማድረግና በየወሩ ለተነሳለት ቆሻሻ ማረጋገጫ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

፭. ማንኛውም ተቋም ወደ ማስወገጃ ቦታ ወይም ማቃጠያ ማዕከላት እንዳይገቡ የተከለከሉ ደረቅ ቆሻሻዎችን ቀላቅሎ ማስቀመጥ የለበትም፡፡

## ፳፫. የተጠያቂነት ስርዓት

- ማንኛውም አካል በዚህ መመሪያ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ካልፈፀመ በህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ፳፬. መመሪውያውን ስለማሻሻል

- ይህ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ በኤጀንሲው ሊያሻሻል ይችላል

## ፳፭. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

- ይህ መመሪያ ከዛሬ 03/07/2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**በአዲስ አባባ ከተማ አስተዳዳር**

**የደረቅ ቆሻሻ አስተዳዳር ኤጀንሲ**